CONGREGATIO PRO CLERICIS

SYNODUS EPISCOPORUM

ቫቲካን, መጋቢት 10 ቀን 2014 ዓ.ም.

ቁጥር. 220083

ውድ ካህናት

እነሆ እኛ ሁላችንንም የሚመለከት ርዕስ ጉዳይ ልናወያያችሁ ወድደን ጥቂት ጊዜያችሁን የምንጠይቃችሁ ወንድሞቻችሁ ሁለት ካህናት ነን።

"የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ለሲኖዶስ ተጠርታለች"። የሲኖዶስ 2021-2023 የዝግጅት ሰነድ የሚጀምረው "ለሲኖዶሳዊት ቤተክርስቲያን፡ አብሮነት፣ ተሳትፎ እና ተልእኮ" በሚል መሪ ቃል ነው። መላው ሕዝበ እግዚአብሔር ለሁለት ዓመታት በእዚህ ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ተጋብዘዋል። ይህ ጉጉትንም ግራ መጋባትንም ሊፈጥር የሚችል አዲስ ነገር ነው።

ሆኖም "በመጀመሪያው ሺህ ዓመት 'በጋራ መጓዝ' ማለትም ሲኖዶሳዊነትን መለማመድ የቤተክርስቲያን የተለመደ የሕይወት መንገድ ነበር። የሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ ይህንኑ የቤተክርስቲያን ሕይወት ጎላ አድርጎ አሳይቷል፣ ስለዚህም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ቤተክርስቲያን እና ሲኖዶስ ሊነጣጠሉ የማይችሉ ናቸው" (*Explicatio in Psalmum* 149) በማለት በአጽንዖት አስተምሯል።

የዛሬው ዓለም ወንድማማችነት እጅግ የሚያስፈልግበት ወቅት መሆኑ ይታወቃል። ዓለም ወንድማማችነትን በአግባቡ ሳትገነዘብ ኢየሱስን ለመገናኘት ትናፍቃለች። እኛስ ወንድማማችነት እንዲሰፍን ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? እምነታችንን ለማደስ፣ ለወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ወንጌልን የምንሰብክበትን አዳዲስ መንገዶች እና ቋንቋዎችን ለመፈለግ ከመላው የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ሆነን መንፈስ ቅዱስን ማዳመጥ ያስፈልገናል። ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራቸስኮስ ያቀረቡት የሲኖዶስ ሂደት ቀጥተኛ ዓላማም ይኸው ነው። በአንድነት፣ እርስ በእርስ በመደማመጥ፣ ሀሳቦቻችንን እና ልምዶቻችንን በመለዋወጥ፣ የቤተክርስቲያኒቱን እውነተኛ ገጽታ ማሳየት፤ ጌታ የሚኖርባት እና በወንድማማችነት መንፈስ የታነጸች፣ በሮቿ የተከፈቱ፣ እንግዳ ተቀባይ የሆነች "ቤት"።

በርእሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስ በተገለጹት ፈተናዎች እንዳንወድቅ እንጠንቀቅ እነርሱም "Formalism" ማለትም ሲኖዶሱን ወደ የተለመደ ስብሰባነት የሚቀንስ ሂደት፣ ወይንም intellectualism ሲኖዶሱን የልሂቃን የችግር መፍቻ ንድፈ ሃሳቦች ብቻ የሚንጸባረቁበት የትምህርት መድረክ ማድረግ እና immobilism ምንም ዓይነት ለውጥ በሚፈራበት የልማድ ችንካር ተቸንክረን መንቀሳቀስ አለመቻል ናቸው። ልባችንን መክፈት እና መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ማዳመጥ አስፈላጊ ነው (ራዕ. 2:7)።

በዚህ ጉዞ ላይ ፍርሃት ሊገጥመን እንደሚችል ግልጽ ነው።

ከሁሉ አስቀድሞ፣ በብዙ የዓለም ክፍሎች ያሉ ካህናት ትልቅ ሐዋርያዊ ሸክም እንደተሸከሙ በሚገባ እንገነዘባለን። አሁን ደግሞ አንድ ተጨማሪ "ኃላፊነት" እንደተጨመረብን ሊሰማን ይችላል። ተጨማሪ ተግባራትን እንድታከናውኑ ከመጋበዝ ይልቅ፣ ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስ በEvangelii gaudium (ቁጥር 71) የነገሩንን መሰረት በማድረግ በየማህበረሰቦቻችሁ እስካሁን በሚደረጉ ተሳትፎዎች የማህበረሰቦቻችሁን በርካታ የሕይወት አብነቶች እንድትመለከቱ ልናበረታታችሁ እንወዳለን።

የሲኖዶስ ዝግጅት ሰነዱ እንደሚያስረዳው በሰበካ ደረጃ በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ ያለው ሂደት ዓላማው "በዕለት ዕለት ኑሮ የሚገለጹ የአብሮነት ጉዞ ተሞክሮ ሃብቶችን ማሰባሰብ ነው" (የዝግጅት ሰነድ 31) ። ገና ከጅምሩ ከምትጠብቋቸው በላይ የሆኑ በርካታ አብሮ የመኖር ተሞክሮዎች እንደሚገጥሟችሁ እርግጠኞች ነን። በጥልቅ በምንደማመጥባቸው፣ እርስ በእርሳችን በምንማርባቸው፣ የሌሎችን ስጦታዎች በምንቀበልባቸው፣ በምንረዳዳባቸው እና ውሳኔዎችን በጋራ በምናሳልፍባቸው ጊዜያቶች ሁሉ ሲኖዶሳዊነት በተግባር ይገለጻል። የሲኖዶስ ዘይቤ እየጎለበተ እንዲሄድ እነዚህ ሁሉ አጽንዖት ሊሰጣቸው እና ለበረታቱ የሚገባቸው ነገሮች ናቸው (የዝግጅት ሰነድ, 10)።

ነገር ግን ተጨማሪ ሌላ ፍርሃትም ሊኖር ይችላል። ሁላችንም በመጠመቃችን ምክንያት ለምንጋራው የክህነት ሕይወት ትኩረት ከተሰጠ፣ የእኛ የካህናት፣ እንደመሪዎች ሚናችን ምን ይሆናል? ሚናችን ያለምንም ጥርጥር የተጠመቁ ሁሉ የሚጋሩትን መሠረታዊ እኩልነት በሂደት መረዳት እና ሁሉም ምእመናን በቤተክርስቲያኑ ጉዞ እና ተልእኮ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ

እንዲያደርጉ ማበረታታት ነው ። በዚህ መንገድ የወንጌል አገልግሎት ኃላፊነትን አብረውን የሚካፈሉ ወንድሞችና እህቶች በማግኘት ደስታን እናገኛለን። ነገር ግን በዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሕይወት ተሞክሮ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል፣ ለመቀደስ እና ለማነጽ የተቀበ ካህናት አገልግሎት በአዲስ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፤ ይገባልም።

በዚህ መንፈስ እየተካሄደ ላለው የሲኖዶስ ሂደት ሦስት ገጽታዎች ያሉት አስተዋፅኦ እንድታበረክቱ እንጠይቃችኋለን

የጋራ ጉዞው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት እና በመኖር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ። ርዕሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስ በቅርቡ እንደመከሩን "የቅዱሳት መጻሕፍት ፍጹም ፍቅር በልባችን ይደር፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ዘወትር አዲስ መሆኑን በሚገልጽልን እና ሳንታክት ሌሎችን ወደ መውደድ በሚመራን በቃሉ እንድንነካ እንፍቀድ" (ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስ እ.አ.አ. እሑድ ጥር 23 ቀን 2022 ስለእግዚአብሔር ቃል ካስተማሩት)

(Francis, Homily for Word of God Sunday, January 23, 2022)።

በቃሉ ሕይወት ካልተመሰረተን በጨለማ ውስጥ በመራመድን አስተዋጽዖዎቻችን ሁሉ ርዕዮተ ዓለም ብቻ ይሆናሉ፤ አደጋ ላይም እንወድቃለን። ይልቁንም ራሳችንን በተግባር በተገለጠው ቃል ላይ በመመሥረት ቤቱን በዓለት ላይ እንገንባ (ማቴ. 7፡24-27)። በዚህም እንደ ኤማሁስ ደቀ መዛሙርት አስደናቂውን ብርሃን እና ሞትን ድል ያደረገውን ጌታ ምሪት ማግኘት እንችላለን።

ጉዟችን በመደማመጥና በመቀባበል ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለማረጋገጥ እንትጋ። ከማናቸውም ተጨባጭ ውጤቶች አስቀድሞ ጥልቅ ውይይት እና እውነተኛ ግንኙነቶች የበለጠ ዋጋ የሚሰጣቸው ነገሮች ናቸው። እንደ እውነቱ ከሆነ በማህበረሰባችን ውስጥ ብዙ ተነሳሽነቶች እና አቅሞች አሉ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ግለሰቦች እና ቡድኖች በግላዊነት እና በእኔነት ስሜት ይጠቃሉ። በአዲሱ ትእዛዙ፣ ኢየሱስ "እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፣ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ" (ዮሐ. 13፡35) በማለት ያሳስበናል። እንደ እረኝነታችን ፍቅር ግንኙነቶችን እና በቤተክርስቲያናችንን የሚያስቃዩ ቁስሎችን እንዲፈውስ ብዙ ማድረግ እንችላለን። አንድ ቤተሰብ፣ አብረን የምንጓዝ፣ ወንድም እና እህት የሆንን የአንድ አባት ልጆች በመሆናችን የሚሰማን ደስታ በከካህናት ወንድማማችነት ይጀምራል።

• ጉዞው ወደ ወደራሳችን ዓለም እንዳይመራን እንጠንቀቅ ይልቁንም ሁሉንም ሰው ለመገናኘት ከራሳችን ዓለም እንድንወጣ የሚያነሳሳን እንዲሆን እናድርግ። የወንጌል ደስታ (Evangelii gaudium) በተሰኘው መልዕክታቸው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቸስኮስ በሰው ልጆች ቁስል ውስጥ በመሳተፍ እጇን ለማቆሸሽ የማትጸየፍ ቤተክርስቲያንን፣ ድሆችን እና የተገለሉትን በማዳመጥ እና በማገልገል ላይ የምትኖር ቤተክርስቲያንን እንድናልም ዐደራ ብለውናል። ይህ በወንድሞቻችን እና በእህቶቻችን ላይ የሚኖረን ስሜት በእግዚአብሔር ቃል መሪነት እና በፍቅር ሥራ እሳት "ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ" (ዮሐ. 17፡21) የሚለው የእግዚአብሔር እቅድ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል። ርእሠ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስ ከሌሎች አብያተክርስቲያናት ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን፣ ከሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች እና በጎ ፈቃድ ካላቸው ሰዎች ጋር ማንም በማይገለልበት፣ ሁሉም ነገር እና እያንዳንዱ ሰው ለሚታቀፍበት ዓለም አቀፋዊ ለሆነ ወንድማማችነት እና ፍቅር እራሳችንን እንድንሰጥ "ሁላችንም ወንድማማቾች ነን" "Fratelli Tutti" በተሰኘው ሐዋርያዊ መልዕክታቸው ጠይቀውናል። እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋዮች ይህ የሲኖዶሳዊ ጉዞ የዝግጅት ሰነድ ግልጽ ያልሆነ እና መመሪያ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ይልቁንም በምንኖርበት አካባቢ ተጨባጭ ውጤት የሚያመጣ እንዲሆን እንድናደርግ በልዩ መብት ተጠርተናል።

ውድ ወንድሞቻችን ካህናት ከእነዚህ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች በመነሳት እንደየአካባቢው ፍላጎቶች እና ሁኔታዎች ለሚከሰቱ መነሳሳቶች ሕይወት የምትዘሩበትን መንገድ እንደምታገኙ እርግጠኞች ነን። ሲኖዶሳዊነት በሦስተኛው ሺህ ዘመን ለምትኖረው ዓለም የቀረበ የእግዚአብሔር እውነተኛ ጥሪ ነው። እንደዚህ በመሰለው አቅጣጫ መጓዝ ፈጽሞ ከጥያቄዎች፣ ከድካም እና እንቅፋት የፀዳ ሊሆን አይችልም፣ ነገር ግን በወንድማማችነት እና በሰብከተ ወንጌል ሕይወት ፍሬ መቶ እጥፍ እንደሚመለስልን እርግጠኞች መሆን እንችላለን። የመጀመሪያውን የኢየሩሳሌም ሲኖዶስ ማሰብ አስፈላጊ ነው (ሐዋ. 15)። ከመጋረጃው በስተጀርባ ምን ያህል ድካም እንደነበረ ማን ያውቃል? ነገር ግን ያን ጊዜ ገና ጀማሪ ለነበረችው ቤተክርስቲያን ምን ያህል ወሳኝ እንደነበረ እናውቃለን።

ይህንን ደብዳቤ ከመሰናዶ ሰነዱ ላይ በወሰድናቸው ሁለት ምንባቦች እናጠቃልላለን።

በተቀበለችው ተልዕኮ መሰረት ስለ ቤተክርስቲያን እና ስለ ተቋሞቿ ልዩ ተስፋን መሰነቅ የሚቻለው በዋናነት እያንዳንዱ ሰው የሚሳተፍበትንና አስተዋጽዖ የሚያደርግበትን የመወያየት እና ማሕበራዊ ግንዛቤ የማዳበር ሂደቶችን ለመጀመር በሚወሰነው ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ ነው። (n. 9)

የሲኖዶሱ ዓላማ ሰነዶችን ለመቀመር ሳይሆን "ህልሞችን ለመትከል, ከትንቢቶች እና ራዕዮች ለመማር, ተስፋን ለማለምለም፣ መተማመንን ለመቀስቀስ፣ ቁስሎችን ለመጠገን፣ ግንኙነቶችን ለማጠናከር የተስፋ ወጋገን እንዲበራ ለማድረግ ከእርስ በእርስ ለመማማርና አእምሮን የሚያበራ፣ ልብን የሚያሞቅና ለእጆቻችን ጥንካሬን የሚሰጥ ብሩህ አእምሮ ለመፍጠር ነው ። (ቁ. 32)

ጊዜያችሁን ስለሰጣችሁን እያመሰገንን፣ ዘወትር በጸሎታችን ከእናንተ ጋር እንደምንሆን ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን። ለእናንተ እና ለማህበረሰቦቻችሁም አስደሳች እና ፍሬያማ የሲኖዶስ ጉዞ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን። በጉዟችሁ አብረናችሁ መሆናችንን እየገለጽን በእኛ በኩል ዘወትር ስለ እናንተ የሚያስቡትን የርዕሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስን ሰላምታ እናቀርብላችኋለን። እያንዳንዳችሁን መልካም መንገድ ለሆነችው ለድንግል ማርያም አደራ እየሰጠን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምታ እናቀርብላችኋለን።

ማሪዮ ካርድ. ግሬች
የጳጳሳት ሲኖዶስ ጠቅላይ ጸሐፊ

✠ ሊቀጳጳሳት ላዛረስ ዩ ሄዉንግ ሲክ
የማኅበረ ክህነት ሐዋርያዊ አስተዳዳሪ